የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ኅዳር ፲፬/፪ሺ፲ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.13
Addis Ababa November 23rd, 2017

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፹፱/፪ሺ፲
የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት
ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ .....ገፅ ፩ሺ፻፺

## CONTENT

Addis Ababa City Resilience Project Office
Establishment Regulation…………Page 1190

## ደንብ ቁጥር ፹፱/፪ሺ፲
## የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ

አዲስ አበባ የሃገሪቱ ዋና ከተማ እና ፳፭ ከመቶ ለሚሆኑት የሃገሪቱ ከተማ ነዋሪዎች መኖሪያ በመሆኗ፣ በመጪዎቹ ፲-፲፭ ዓመታት የከተማዋ ህዝብ ብዛት እጥፍ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን ይህም በ፪ሺ፳፭ መካከለኛ ገቢ ሀገር ለመሆን ለምትመኘው ሀገር ተግዳሮትንና መልካም አጋጣሚዎችን የሚሰጥ በመሆኑ፣

## REGULATION NO. 89/2017
## THE ADDIS ABABA CITY RESILIENCE PROJECT OFFICE ESTABLISHMENT REGULATION

**WHEREAS**, Addis Ababa is the country's capital and home to 25% of the country's urban population,the city's population is expected to double in the coming 10 to 15 years bringing both challenges and opportunities to a country aspiring to be a middle income economy by 2025;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ከተማዋ የኢትዮጵያ የዕድገት አንቀሳቃሽ እንደመሆንዋ የሃገሪቱን ፍላጎት ለማርካት በመሠረተ ልማት፣ በቤቶችና በማህበራዊ ግልጋሎቶች መስጫዎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ በማካሄድ ላይ ስለምትገኝ፣

ምንም እንኳን እነዚህ ሁሉ ጥረቶች እየተከናወኑ ቢሆንም ከተማዋ ቀጣይነት ያለው የእድገት አቅጣጫዋን የሚፈታተኑ ድንገተኛ ክስተቶችና ጫናዎች እያጋጠሟት ስለሚገኙ፡ እነዚህን ተግዳሮቶች ተደራሽ ለማድረግ የከተማዋን የአደጋ ተቋቋሚነት አጀንዳን እና እያደገ በመምጣት ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎት ለማሟላት ከተማዋ የምታደርገውን ጥረት ለመምራት የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፫ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፹፬ መሰረት ይህን ደንብ አዉጥቷል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፱/፪ሺ፲ ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::



Being a growth engine for Ethiopia, the city is undergoing massive transformation including infrastructure, housing and social facilities;

However, despite all these efforts, the city faces several kinds of shocks and stresses which impacts the cities sustainable growth trajectory;

To address these challenges, it has become necessary to establish a project office which will guide the city's resilience agenda to cope with and cater for the ever growing economic and social demands by being resilient against the cities shocks and stresses;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 23 sub-article (1)(f) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No.361/2003 (as amended), and the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No 35/2004 (as amended) Article 84, the Addis Ababa City Government Cabinet issued this regulations as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the <<Addis Ababa City Resilience Project Office Establishment Regulation No 89/2017. >>

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፫. “**ስቲሪንግ ኮሚቴ**” ማለት ከተለያዩ መስሪያ ቤቶችና ባለሙያዎች የተወጣጡ አባላት ያሉበትና በከንቲባዉ የሚሰየም የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤትን በበላይነት የሚያማክር አካል ነው፡፡

፬. “**ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት**” ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ነው::

፭.“**ሬዚሊየንስ**” ማለት በከተማ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች፣ ተቋማትና ድርጅቶች ማንኛውንም የሚገጥማቸውን ብርቱ ችግርና ጫና ለመቋቋም፣ ለመላመድና ሰብሮ ለማለፍ የሚያስችላቸው አቅም ማለት ነው፡፡

## ፫. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ዉስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፬. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደሩ ክልል ዉስጥ ለተመረጡ ብርቱ ችግርና ጫና ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

## 2. Definition

Unless the context requires otherwise , in this regulation

1. <<**Government** >>means Addis Ababa City Government.
2. <<**City**>> means Addis Ababa City.
3. <<**Steering Committee**>> means a higher advisory body of the project office comprising of members from different offices and professional designated by the mayor.
4. <<**Project Office**>> means the Addis Ababa City Resilience Project Office.
5. <<**Resilience**>> means the capacity of individuals, communities, institutions, businesses, and systems within a city to survive, adapt, and grow no matter what kinds of chronic stresses and acute shocks they experience.

## 3. Gender Reference

Provisions of this Regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 4. Scope of application

This regulation shall be applicable based on the stresses and shocks that are identified in City Government.

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም ፣ተጠሪነት፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

**፭. መቋቋምና ተጠሪነት**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ሬዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት") እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪. የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት ይሆናል::

**፮ አደረጃጀት**

**የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ፡-**

፩. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱን በበላይነት የሚያማክር (ከዚህ በኋላ "ስቲሪንግ ኮሚቴ") እየተባለ የሚጠራ፣

፪. ዋና ስራ አስኪያጅ፣

፫. የቴክኒክ ባለሙያዎች፣

፬. ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል::

**፯ ዋናመስሪያ ቤት**

የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል::

**፰ የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

## PART TWO

## ESTABLISHMENT,ACCOUNATIBILITY, ORGANIZATION,POWER AND FUNCTION

**5. Establishment And Accountability**

1. The project office shall be established as an autonomous natural person in this regulation.

2. The project office shall be accountable to the Office of the Mayor.

**6. Organization of the project office**

The project office shall have:

1. A high level advisory committee (here in after referred to as the "steering committee>>);
2. General manager;
3. Technical experts; and
4. other necessary workers and work divisions.

**7. Head office**

The head office of the project office shall be in Addis Ababa.

**8. Power and function of the project office**

The project office shall have the following power and functions:

፩. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ይበልጥ ሬዚሊየንት ለሆነች ከተማ አቀፍ ስትራቴጂ ይነድፋል::

፪. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ለሬዚለንት እስትራቴጂ ትግበራ ከተለያዩ የሀገር ውስጥ፣ የክልል እና የውጭ ሀገር እንዲሁም የግል ዘርፍ አካላት ጋር አጋርነትን ይመሰርታል::

፫. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ለሁሉም ዘርፎች የሬዚለንስ ስትራቴጂን ለማስፈጸም አዋጪ ፕሮጀክቶችን ያሰናዳል፤ ለተፈፃሚነታቸውም ተዛማጅ የሆነ የገንዘብ ምንጭ መገኘቱን እና ለታለመለት ዐላማ መሰራጨቱን ያረጋግጣል፡፡

፬. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በከተማዋ ውስጥ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማቀናጀትና በማስተባበር ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት የተጠናከረ መረጃ ያቀርባል::

፭. ለሬዚለየንስ ስትራቴጂው ትግበራ የሚውል የሀብት ማሰባሰብን ለማመቻቸት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በአዲስ አበባ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስር የሚተዳደር የሬዚሊየንስ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

፮. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በሬዚለየንስ አግባብ ፍላጎት መርና ችግር ፈቺ የሆነ ጥናትና የተጽእኖ ዳሰሳን ከዩኒቨርሲቲ፣ ከምርመር ማዕከላት እና ከሌሎች ትምህርታዊ አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፡፡ ውጤቱ የከንቲባ ጽሕፈት ቤት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ እንደግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡

1. The project office will lead the design and development of the city resilience strategy.

2. The project office will play an important role in establishing partnerships with different local, regional and international organizations and the private sector for the execution of the resilience strategy.

3. The project office will develop bankable project proposals for all sectors thereby securing funding for implementation by the respective sectors. It will also follow-up the disbursement of the funds for the intended objective.

4. The Project office will coordinate and consolidate the different projects in the city there by providing relevant consolidated data for the Mayor's office.

5. To facilitate the resource mobilization for the implementation of the resilience strategy, the project office will establish a resilience facility under the Bureau of Addis Ababa Finance and Economic Development.

6. The Project office will Conduct resilience tailored demand driven and problem solving research and impact studies by collaborating with local and international universities, academia, research institutes and others which will be an important input for decision by the Mayor's office.

**፱. የስቲሪንግ ኮሚቴ አሰያየም**

፩.የስቲሪንግ ኮሚቴው አባላት በከተማው ከንቲባ ይሰየማሉ፡፡

፪. ስቲሪንግ ኮሚቴው ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ተቋማትና ባለሙያዎች የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል::

፫. የስቲሪንግ ኮሚቴው ተጠሪነት ለከተማው ከንቲባ ይሆናል::

**፲.የስቲሪንግ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር**

፩.ፕሮጀክቱ ከተገቢ ሀገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ህግጋት ጋር በአንድ ላይ እንደሚሔድ ማረጋገጥ፤

፪.የሬዚሊየንስ ስትራጂውን ዝግጅት እና ትግበራ በሚገባ ማስፈጸም፤

፫. የስራ ዕቅዶችን መከለስና ማረጋገጥ፤

፬. የፕሮጀክት ትግበራ ስጋቶችን እና ተግዳሮቶችን በመለየት ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ፤

፭. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስቲሪንግ ኮሚቴውን ስራ የሚያግዝ የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም::

**፲፩. የስቲሪንግ ኮሚቴው ስብሰባ**

፩.ኮሚቴው በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡

፪.የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ከአባላቱ አንድ ሥስተኛው ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል::

**9. Appointment of the steering committee**

1. The members of the steering committee shall be designated by the mayor of the city.
2. The steering committee shall have members from the concerned institutions and professionals.
3. The steering committee shall be accountable to the Mayor of the City of Addis Ababa.

**10. Power and function of the steering committee**

1. Ensure that the Project is aligned with relevant country and city policies, strategies and laws;
2. Oversee the development and implementation of the resilience strategy ;
3. Monitor and review the progress of the implementation of the Project;
4. Identify project implementation risks and challenges and take corrective measures, where appropriate;
5. Assign technical Committee to support the work of the committee when deemed necessary.

**11. Meetings of the Steering Committee**

1. Steering Committee Shall conduct its regular meeting quarterly.
2. Emergency meeting may be called up on the request of the chairperson or by one third of the member.

፫.የኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::

፬.ማንኛውም የኮሚቴ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በድምፅ ብልጫ ሆኖ ድምፁ እኩል ከሆነ የኮሚቴው ሰብሳቢ የደገፈዉ ወገን ሀሳብ የኮሚቴው ዉሳኔ ይሆናል::

፭.ኮሚቴው የራሱ የስነስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

3. The quorum may be constituted if morethan half of the members presented.
4. Any decision of the committee shall be passed by majority vote of the members participated in the meeting; if the total number of votes equal the decisions of the committee shall be the decision of the members supported by the chairperson of the steering committee.
5. The steering committee may issue its own procedural directives.

## ፲፪. የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

፩. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ሰራተኞችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል::

፪. ለፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል::

፫. ወቅታዊና አመታዊ ሪፖርት ለኮሚቴው እና ለሚመለከተው አባል ያቀርባል::

፬. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱን በመወከል ከሦተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል::

፭. የፕሮጀክት ጽሐፍት ቤቱ የውስጥ መመሪያዎች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል::

## 12. Power and function of the general manager of the project office

1. The general manger shall, as superior body, administer the project office and recruit and fire employees in accordance with the appropriate law.
2. The project manager shall prepare and submit annual work plan and budget to the appropriate organ for approval; will make sure its implementation according to its approval.
3. The general manger shall submit periodical and annual report to the steering committee and the body it may concern.
4. The general manger shall make relationship with third party by representing the project office.
5. The general manger enable internal directives of the project office to be issued, scrutinized, if approved implement it.

## ክፍል ሶስት

## የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በጀት፣ የሒሳብ መዛግብት ፣ ንብረት እና የሰው ሀይል አስተዳደር

### ፲፫. በጀትና የሒሳብ መዛግብት

፩. የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ አስተዳደራዊ በጀት በአስተዳደሩ ይመደባል::

፪. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና የተረጋገጡ የሒሳብ መዛግብት ይኖሩታል::

፫. የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የሒሳብ መዛግብትና ሰነዶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ እና እንዳስፈላጊነቱ በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እሱ በሚወክለው ተቋም ይመረመራል::

### ፲፬.ስለ ንብረት አስተዳደር

፩. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የራሱ ንብረቶች ይኖሩታል::

፪. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ንብረቶቹን በኀላፊነት ያስተዳድራል ፣ ይቆጣጠራል::

፫. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የስራ ዘመኑ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹን በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ለሚመለከተዉ አካል ያስረክባል::

### ፲፭.የሰው ሀይል

፩. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በተጠናዉ ጥናት መሰረት የሰው ሀይል መዋቅሩ ሲፈቅድለት ሰራተኞችን በቋሚነት እና በጊዜያዊነት ይቀጥራል::

## PART THREE

## BUDGET,BOOK OF ACCOUNTS, PROPERTY AND HUMAN RESOURCE ADMINISTRATION OF THE PROJECT OFFICE

### 13.Budget and book of accounts

1. The Addis Ababa City Government shall allocate administrative budget to the project office.
2. The project office shall have complete and authenticated book of accounts.

4. Book of accounts and financial documents of the project office shall be examined by the chief auditor office or its appointee office at the end of the fiscal year and deemed necessary.??????

### 14. Property and Administration

1. The project office shall have its own properties.
2. The project office shall administer and control properties thereof.
3. The project office shall deliver properties to the concerned body as per the Financial Administration laws of the City Government up on the closure of the project office.

### 15. Human Resource

1. The project office shall recruit employees on temporary and permanent basis in accordance with the study conducted on the permitted human resource structure

፪. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ለስራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ተጨማሪ ሰራተኞችን ከአስተዳደሩ ቋሚ ሠራተኞች ሊጠቀም ይችላል፤ እንዲሁም ለአጠቃቀሙ መመሪያ ያወጣል::

፫. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ የሬዚሊየንስ ስትራተጂዉን ለማዘጋጀትና ለመተግበር ለአጭር ጊዜም ሆነ ለረዥም ጊዜ አማካሪ ባለሙያዎችን ካሉት ቋሚ ባለሙያዎች በተጨማሪ ቀጥሮ ያሰራል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፮. የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የስራ ዘመን

የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የስራ ዘመን አምስት ዓመታት ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል::

### ፲፯. ስለ መተባበር

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት::

### ፲፰. ደንቡን ስለማሻሻል

ይህንን ደንብ የከተማው ካቢኔ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽለዉ ይችላል::

### ፲፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎችና አሰራሮች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የአስተዳደሩ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

2. The project office may use other additional permanent workers of the City Government to carry out its tasks as may be necessary; and also develop directives how to use permanent workers of the City Government.

3. The project office may hire short term and long term consultants for the preparation of the resilience strategy, project proposal development and for assistance in the implementation stages of the strategy.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 16. Working tenure of the project office

1.The project office will be operational for a period of five years; It could be extended if found necessary.

### 17. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this regulation.

### 18. Amendment

As may be necessary this regulation shall be amended by Addis Ababa City Cabinet.

### 19. Inapplicable laws and practice

Any City Government regulation, directive or practice inconsistent with this regulation shall not apply with the matters provided for in this regulation.

**፳.<u>አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከኅዳር ፲፬ ቀን ፪ሺ፲ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የጸና ይሆናል::

**20. <u>Effective date</u>**

This Regulation shall enter into force as of the 23rd day of November,2017.

**አዲስ አበባ ኅዳር ፲፬ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 23rd day of November,2017.**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**Diriba Kuma**

**Mayor of the Addis Ababa City**